# የፖለቲካ ሽሙጥ

*ከአስተዋይ በቀለ*

*ያልገባው ያቺ የሞኝ ዘፈኑን ብርቱካን ብርቱካን እያለ ይዘፍናል። በድሮ በሬ ያረሰ የለም።*

*ብርቱካን የፖለቲካው መንገድ የጠፋት ገና ድሮ በብርሃኑ አሻጥር ነው። ብርሃኑ ለወንበር ክፉኛ ቋመጠና አገባሻለሁ ያላት ይመስል የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ በላቀ ተስፋ አቅፎና ደግፎ ለድል ያቃረበውን ቅንጅት አብራ ተባብራ አፈረሰች። በሕዝብ ትግል ላይ ውሃ አብራ አፈሰሰች። በጥይት የተገደሉ ሰማዕታት መስዋዕትነትን ከምንም ሳትቆጥር በቅንጅት አፅም ላይ ተረማምዳ ወያኔን በእጅ አዙር አጠናከረች። ይኸ አልበቃት ብሎ በቅሌታም ሽማግሌ ተብዬዎች ሽፋን በምስጢር ተደራድራ ከቃሊቲ በመውጣት ለወያኔ ሕገ - ወጥ ሕልውናና ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት ሌጅትሜሲ ሰጥታለች።*

*ብርቱካን በባሕሪዋ አፈንጋጭ፣ አንጃኛ፣ ጠባብና አፍራሽ ኃይሎችን የምትስብና አብራ የምታቅፍ ከመሆኗ ጋር በፈረመችው ሰነድ ለወያኔ ሎሌነት ስላደረች ለኢትዮጵያ አንድነትና ለፀረ-ወያኔ ትግል ዋጋ የላትም።*

*አበሻ! አንበሲት፣ ማንዴላ ከማለት ይልቅ እርምህን አውጣ። ትግሉ የሚጠይቀው ለአገርና ለሕዝብ ጥቅም ጥርት ያለ አቋምና በመስዋዕትነት ላይ መስዋዕትነትን ለመክፈል ዝግጁነትን ነው። ብርቱካን ይህን መስፈርት አታሟላም።*

*በአገርና በሕዝብ ቀልድ የለም። አመለካከታችን እናስተካክል። አሰላለፋችንንም በውል እንለይ።*

*ለአገር ከሃቀኞችና የፖለቲካ ፅናት ካላቸው ጋር መቆም ሕያው የሆነ ፀጋና ብሔራዊ ክብር ነው።*